# AMHARIC

**ጥልቅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተቋም**

የክሬይተን ዩንቨርስቲ ጥልቅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተቋም ከ1979 ዓ.ም(እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር) ጀምሮ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ሥልጠና በመስጠት እየረዳ ይገኛል:: እነዚህ ሥልጠናዎች በትምህርት ቤት አስፈላጊ በሆኑ የእንግሊዘኛ ሠዋስዉ÷ መፃፍ÷ማንበብ እና መናገር/ መስማት ክህሎቶች ላይ ያተኩራሉ::

የትምህረት ክፍለ ጊዜው ከሰኞ እስከ አርብ (ከጠዋት 9:00 ኤም እስከ 3:00ፒም)÷ በየቀኑ ለአራት ሰዓት ነው:: በተጨማሪ የተለየ ጊዜ የተመደበላቸው የጎን ለጎን ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሆኑ ክፍለ ጊዜዎች ይኖራሉ:: ይህ ሥልጠና በበልግ (ፉል) እና ፀደይ(ስፕሪንግ) ሴመስተር የ17 ሳምንት ሲሆን÷በክረምት (ሠመር) የተፋጠነ 9 ሳምንት ሥልጠና ነው:: ይህ ሥልጠና 4 እርከን አለው÷ እነዚህም ጀማሪ÷መካከለኛ÷ ከፍ ያለ መካከለኛ እና ከፍተኛ ናቸዉ::

**የክሬይተን ዩንቨርስቲ ጥልቅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተቋም ተልዕኮ:**

1. ጥልቅ የእንግሊዝኛ ትምህርት መስጠት እና የጥልቅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተቋም ተማሪዎች በክሬይተን ዩንቨርስቲ ለሚያስፈልገው የትምህርት(አካዴሚክ) ብቃት  የሚያስፈልገውን ድጋፍ እና ዝግጅት መስጠት::
2. የእንግሊዘኛ ቋንቋ አጠቃቀምና የሥነፅሑፍ ሥራዎች ትምህርትን በታማኝነት እና ትህትና በተሟላበት ሁኔታ መተግበር::
3. የባህል ከባህል ተራክቦ መረዳትን÷ በትምህርት ቤት ግቢ እና በማህበረሠብ ተሳትፎ÷ እና በዓለም አቀፍ ዜግነት ላይ መሪ ደጋፍ መስጠት::
4. የክሬይተን ዩንቨርስቲ ተልዕኮ ማንፀባረቅ እና መደገፍ::

**ድልድይ ወደ ክሬይተን**

ድልድይ ወደ ክሬይተን ለየት ያለ ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው:: ይህ ፕሮግራም ትልቅ የትምህርት አቅም ያላቸውን ተማሪዎች በተጨማሪ የላቀ (ከፍተኛ) ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ሥልጠና ለመርዳት የተቀረፀ መርኃግብር ነው:: ድልድይ ወደ ክሬይተን ከእንግሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርኀግብር በላይ ነው:: ድልድይ ወደ ክሬይተን አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያሟሉ ተማሪዎች 6 ክሬዲት  በክሬይተን የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት መርኃግብር እንዲያገኙ ይፈቅዳል÷ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ደረጃ ባለው ዩኒቨርሲቲ  ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ይሰጣል::

በድልድይ ወደ ክሬይተን ከፍተኛ ብቃት ያላቸው የጥልቅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተቋም መምኅሮች ተማሪዎችን በወሳኝ ንባብ (በጥልቀት ማንበብ እና በማሰላሰል) መርኆች÷ በትምህርት ላይ የሚዘወተሩ ቃላቶች÷ ከፍተኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ሠዋስው÷ የማቅረብና በሰው ፊት ኀሳብን የመግለፅ/የማውራት እና መግባባት ክህሎትዎች እና የማስታወሻ አወሳሰድ ላይ ሥልጠና ይሰጣሉ::
የ3 ክሬዲት የመፃፍ ትምህርት(ኮርስ) ተማሪዎች
በክሬይተን ትምህርት ወስተ ለሚያጋጥማቸው የፅሁፍ የታቀደ ሥራ (ፕሮጀክት) አስፈላጊውን መልመጃ እና መመሪያ ይሰጣል:: የ2 ክሬዲት አካዳሚያዊ ስኬት (ስኬማነት በትምህርት) ትምህርት (ኮርስ) በክሬይተን ግቢ ያሉ የተለያዩ አገልግሎቶችን ያስተዋዉቃል:: በመጨረሻ የ 1 ክሬዲት ትምህርት(ኮርስ) ተማሪዎችን ከአጋዥ እና መካሪ መምህሮች ጋር ያገናኟል÷በተጨማሪ ውስን የተማሪዎች ቡድን በክሬይተን ዩንቨርስቲ የግቢ ህይወት ያሉ ወሳኝ ሁነቶችን እንዲያዩና እንዲመረምሩ ያመቻቻል::

ወደ ድልድይ ወደ ክሬይተን መርኀግብር ለመግባት  በቶፍል ፈተና 68  ወይም በአይኤልቲስ ፈተና 6.0 እንዲሁም የክሬይተን ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ መርኃግብር የአመልካች ቅድመ ሁኔታዎች እና ማመልከቻ ሟሙዋላት ያስፈልጋል::